## ❖ ህልውና እና ክህደት … ?

… ኤርትራን ጨምሮ በሀገራዊ ታሪካቸው ደርዝ ከእኛ በእጅጉ ያነሰ ዕድሜና ቅርስ ያላቸው ሀገሮች በኃይል የደፈሩን፤ በጦር ባይደፍሩንም ተፅዕኖ የሚያሳርፉብን፣ ከፍም ሲል እንደ ህዝብና ሀገር የሚንቁን ለምንድነው? በበቂ ደረጃ የታየና በተደጋጋሚ ያስመሰከርነው ሲደፈሩ እምቢኝ ብሎ በጀግንነት የመዋጋት የነፃነት ታሪክ ስላነሰን? ወይስ ይህ ማንነታችንና ታሪካችን ሊሸፍነው ያልቻለ ተመፅዋችነታችን እና ድህነታችን? በዛሬ ፊት ያኮሰሰንና የገናና ታሪክ ባለቤትነታችንን በጥርጣሬ እንዲታይ ያደረገው የገዘፈው ድህነታችን ወይስ የጀግንነት ገድል በታሪካችን ያነሰ መሆን? … ወደፊት ሊያጋጥመን የሚችል *መደፈር ማድረቅ የሚያስችል መንገድን መከተል፣ ወይስ ''ህፃን ልጁን በጣም ከመውደዱ የተነሳ አቅፎ የሚገድል የማይጥም የጅል ፍቅር''* እንደተባለው የደርግ አካሄድ ሁሉን ነገር *የሚያጠፋ የጦርነት መንገድ ውስጥ መግባትና መዳከር? የዘላቂ ብሔራዊ ጥቅም ማስከበሪያ መንገድስ* የትኛው ነው? የቱስ ነው ክህደት? …

… ካለንበት እውነታ አኳያ ለምርጫ የማይቀርብ፣ እንደህዝብና ሀገር ህልውናችንን ይዞ ለመጥፋት (በኤርትራም ተደፍረን ሆነ በሌላ) ዋነኛ ምክንያት የሚሆነው በተወሰኑ መሬቶች ላይ ከኤርትራ ጋር መደራደራችን ወይስ ድህነታችን? በኤርትራስ የተወረርነው ንግግር ወይም ድርድር እምቢ ስላልን? ትንሽ ብሔራዊ ኩራት ስላለን? ብሔራዊ ጥቅማችንንና ሉዓላዊነታችንን ለመስጠት ፈቃደኞች ነን ብለን ስላወጅን? ወይስ አቅም የላቸውም በሚል ግምትና ግምገማ? ከወረራው በኋላ ፍትሓዊ አይደለም ያልነውን የድንበር ኮሚሽን ውሳኔ እንድንቀበል በተለያዩ ኃይሎች የምንገፋው ለምንድነው? በግልባጩም ይህንን ፍትሓዊ አለመሆን በቀጥታ በማስቀመጥ እምቢ ማለት አቅቶን የተለያዩ ዲፕሎማሲያዊ አክሮባቶችን እንደ ሀገርና መንግስት ለመስራት የተገደድነው መርጠንና ፈልገን ወይስ ''ዳገቱን የማይወጣ አቅም ስላለን''? …

------------------------------ /// ------------------------------

***… አፄ ምኒልክም ሆኑ አፄ ኃይለሥላሴ የተሻለ ያሉትን ሰፊውን የኢትዮጵያ ክፍል አንድ ሆኖ የመቀጠል ጥቅም መርጠው፣ እነዚህን ሁኔታዎች ተቀብለው ባይጓዙ ኖሮ ለዛሬዋ ኢትዮጵያ እንበቃ ነበር ወይ? አፄ ኃይለሥላሴም ሆኑ ምኒልክ በዚህ ሂደት ያደረጉትን አንድ ድርጊት (ኤርትራ ከኢትዮጵያ ውጪ እንድትቆይ መስማማታቸው ወይም ''አካኪ ዘራፍ'' ሳይሉ ዝም ማለታቸውን) ዓይተን ከሀዲ ብንላቸው ተገቢ ይሆናል?? …*** በዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ዋነኛ ከሆኑና በኤርትራ ጉዳይ የሰፉ ሚና ካላቸው መሪዎች ማን ከሃዲ ተብሎ ተፈርጇል? ማንስ በከሃዲነት አልተፈረጀም? ለምን? የከሃዲነት ትርጉምና መስፈርትስ ምንድነው? …